**መስከረም 20፣ 2012 ዓ.ም.**

***ጋዜጣዊ መግለጫ***

## በኢትዮጵያ ቀዳሚና ብቸኛው የእንስሳት ሃብት ተዋፅኦ ዓወደርዕይ የዘርፉን ዋነኛ አንቀሳቃሾችን በማሳተፍ ይካሄዳል

## በ2012ቱ የንግድ ትርዒት ከ50 በመቶ በላይ ተሳታፊዎችን እንዲሁም የዓውደርዕይ ቦታ ዕድገት በማስመዝገብ ይካሄዳል

## ከ10 ሃገራት የተውጣጡ፤ ከአንድ መቶ በላይ የንግድ ትርኢቱ ተሳታፊዎች፤ ከ4000 በላይ ከሚሆኑ የንግድ ትርኢቱ ታዳሚዎች ጋር ጠንካራ የንግድ ልውውጥ እንደሚያደርጉ ይታመናል፡፡

***(አዲስ አበባ)*** **9ኛው የኢትዮ ፖልተሪ ኤክስፖ፣ ከ5ኛው የአፍሪካ እንስሳት አውደ ርዕይና ጉባዔ እንዲሁም ከመጀመሪያው የ አኳካልቸር እና አፒካለቸር ኢትዮጵያ ጋር አንድ ላይ በማድረግ የየዘርፉን ዋንኛ ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ ከመጪው ጥቅምት 6 – 8፣ 2012 ዓ.ም. በሚሌኒየም አዳራሽ ይካሄዳል፡፡**

በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም የንግድ ትርዒቶች አዘጋጅ በሆነው ፕራና ኤቨንትስ እና መቀመጫውን ሱዳን ባደረገው አጋሩ ኤክስፖ ቲም ትብብር ቀዳሚ እና ሁሉን ዓቀፍ የእንስሳት ተዋፅኦ፣ የዶሮ፣ የአሳ እና የንብ ቴክኖሎጂ፣ ግብዓት እና ምርቶች የንግድ ትርዒት ሁሉንም የእንስሳት ሀብት የገበያ ሰንሰለቶች ላይ ያሉ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለማስተዋወቅ፣ የገበያ ትስስር ለመፍጠር እነዲሁም የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማምጣት የዘርፉ ማህበራትን እንዲሁም በ10 ሀገራት መሰረታቸውን ባደረጉ ጠንካራ ድርጅቶች ተሳትፎ ይካሄዳል፡፡

ባለፉት ዓመታት ለተከታታይ ጊዜያት የተካሄዱት ዓውደርዕዮች ለእንስሳት መኖ፣ ወተት፣ ስጋ እንዲሁም ለእንስሳት ጤና ዘርፍ ዕድገትና ልማት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳበረከቱ በውጤት የተረጋገጠ ሲሆን በ2012ቱ ዓውደርዕይ ያለንን ሀብትና የገበያ ዕድል መሰረት በማድረግ የአሳ እና የማር ዘርፍን በማካተት የሚካሄድ ይሆናል፡፡ ለ 3 ቀናት በሚካሄደው ዓውደ ርዕይና ጉባዔ በርካታ የየዘርፉ መሪዎችና ወሳኝ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ አንጻር ላቅ ያለ ስኬት እንደሚመዘገብ ይጠበቃል፡፡

## ሁሉንዓቀፍ የእንስሳት ሀብት የገበያ ሰንሰለት ንግድትርዒት

*የአፍሪካ የእንስሳት ሀብት ዓውደርዕይና ጉባዔ፡* ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ባለቤት ብትሆንም ከዘርፉ ያላት ተጠቃሚነት እምብዛም የሚባል አይደለም፡፡ ይህ የንግድ ትርዒትም የእንስሳት ጤና፣ የእንስሳት መኖ፣ የወተት እና የስጋ ዘርፉን በዘመናዊ መልክ ለማሳደግ ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰራበት መድረክ ነው፡፡

*የኢትዮ ዶሮ ኤክስፖ፡* ባህላዊ የዶሮ እርባታ እስካሁን በስፋት የሚዘወተር ልምድ በመሆኑ ዘመናዊ የዶሮ እርባታን በማስፋፋት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ውስጥ አስፈላጊውን አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚዘጋጅ ብቸኛው የዘርፉ ማስተዋወቂያ ኹነት ነው፡፡

*የኢትዮጵያ የአሳ ኤክስፖ፡* በአለም ላይ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ የሚገኘውን ይህንን ዘርፍ በሀገራችን የሚስፋፋበትን ሁኔታ ለመፍጠር ያስችል ዘንድ ኋላ ቀር የሆነውን የአሳ ዘርፍ በመቀየር ለምግብ ዋስትና አንዱ አማራጭ እንዲሆን ዘርፉ የሚተዋወቅበት ዓውደርዕይ ነው፡፡

*የኢትዮጵያ የማር ኤክስፖ፡* ማር ብቸኛው ወደ አውሮፓ የምንልከው የግብርና ምርት ቢሆንም ሀገሪቱ ካላት ሀብት አንፃር ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ዘርፉን እና ለማዘመን የተጀመረ ፕሮግራም ነው፡፡

## ከ50 በመቶ በላይ ዕድገት በተሳታፊዎች ቁጥር እና የዓውደ ርዕይ ቦታ ስፋት

ከቻይና፣ ኢትዮጵያ፣ ጀርመን፣ ሃንጋሪ፣ ህንድ፣ ጣሊያን፣ ኬንያ፣ ኔዘርላንድሰ፣ ሱዳን እና አሜሪካ የሚመጡ ዓለም ዓቀፍ የዘርፉ መሪዎች እና ጠንካራ የሀገር ውስጥ ኩባንያዎች የሚሳተፉበት ይህ የንግድ ትርዒት 4000ሺህ ከሚበልጡ የዘርፉ ባላድርሻ አካላት ጋር የቴክኖሎጂ ሽግግርን መሰረት ያደረገ የንግድ ልውውጥ እና የኤክስፖርት ገበያ ትስስር ይካሄድበታል፡፡

በ2012ቱ የንግድ ትርዒት በተሳታፊዎች ቁጥር እንዲሁም የዓውደርዕይ ቦታ ስፋት ካለፈው ዓመት የ50 በመቶ ጭማሪ ያሳየ በመሆኑ እንዲሁም በተሳታፊዎች ጥራት እና ብዙሀነት ምክንያት ከፍተኛ ውጤት እንደሚያስመዘግብ ተገምቷል፡፡

በሀገሪቱ ያሉ አብዛኛው የአንድ ቀን ጫጩት እና የተዘጋጁ የዶሮ ምርት አቅራቢዎች እንዲሁም የተመረጡ አርቢዎች ተሳታፊ መሆናቸው የዶሮ ዘርፉን አንድ እርምጃ ወደፊት እንደሚያስመነድገው ይጠበቃል፡፡ በዓውደርዕዩ ወቅት በሚካሄደው ከመዳረሻ ሀገራት ከተጋበዙ ገኚዎች ጋር የሚደረገው የንግድ ልውውጥ መድረክም የሀገሪቱን ኤክስፖርት ሊያሳድገው እንዲመችልም ይገመታል፡፡

## ተቋማዊ ድጋፍ

ይህ የንግድ ትርዒት በመንግስት በኩል በግብርና ሚኒስቴር፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ስጋና ወትት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እንዲሁም በእንስሳት መድኃኒትና የእንስሳት መኖ አስተዳደርና እና ቁጥጥር ባለስልጣን የሚደገፍ ሲሆን በአሜሪካ ዕርዳታ ድርጅት የፊድ ዘፊውቸር የኢትዮጵያ ፕሮጀክት አመኔታ ተጥሎበታል። በኢትዮጵያ ስጋና አምራችና ላኪዎች ማህበር፣ በኢትዮጵያ ዶሮ አርቢዎችና አቀነባበሪዎች ማህበር እንዲሁም በኢትዮጵያ የቁም እንስሳት ላኪዎች ማህበርም አጋርነታቸውን አስቀጥለዋል። በሀዌቱ የእንስሳት መድሀኒትና የህክምና መገልገያዎች አስመጪም ለ2ኛ ጊዜ ስፖንሰር ተደርጓል።

## የእንስሳት ሃብትና የእንስሳት ተዋፅዖ ገበያ እውነታዎች

በኢትዮጵያ የእንስሳት ተዋፅኦ ምርት ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዚ እየጨመረ ቢመጣም፤ የሃገር ውስጥ ምርት አቅርቦት ግን በሚፈለገው መጠንና ጥራት የምርት ፍላጎቱን ማዳረስ አልቻለም። እንደ አለምዓቀፉ የግብርና ድርጅት መረጃ ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2030 456,000 ቶን የከብት ስጋ፣ 14,231 ቶን ወተት, 96,000 ቶን ዶሮ, 54,000 ቶን እንቁላል እንዲሁም 265,000 ቶን የበግና ፍየል ስጋ እንደምትጠቀም ይገመታል።

የነፍስ ወከፍ ፍጆታን ስንመለከት የፋኦ 2016 መረጃ የሚያሳየም የደሮ ስጋ 0.66 ኪ.ግ.፣ እንቁላል 0.36 ኪ.ግ. ሲሆን በተመሳሳይ ዓመት የነበረው የበግና ፍየል ስጋ ፍጆታም 1.4 ኪ.ግ.ብቻ ነው። ይህም በአለም ዝቅተኛ ፍጆታ እንደሆነ መረጃው ያመለክታል።

በ2018 2.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ 3.8 ሚሊየን ሊትር ወተት እንዲሁም 5.1 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ 1 ሚሊዮን ቶን ስጋ በማምረት የእንስሳት ሀብት ዘርፉ ከአጠቃላይ ግብርና 45 በመቶ የሚሆነውን እንደሚሸፍን የአለም የምግብና እርሻ ድርጅት በሪፖርቱ ይገልፃል። የወተት ነፍስ ወከፍ ፍጆታ 19 ኪ.ግ. ሲሆን ስጋ ደግሞ 7 ኪ.ግ. ብቻ መሆኑን ያመለክታል።

አፍሪካ እ.ኤ.አ በ2050 83 ሚሊዮን ቶን የወተት ፍጆታ ይኖራታል ተብሎ ይጠበቃል። በተመሳሳይ በ2050 የስጋ 13.5 እና የዶሮ ስጋ 11.8 ሚሊዮኝ ቶን ፍጆታ ይኖራል። የእንቁላል፤ የአሳማ ስጋና የፍየል ወይም በግ ገበያዎች 6.1፣ 3.5 እና 5.9 ሚሊዮን ቶን እንደሚያሻቅብ ይገመታል። የአሳ ምርት እ.ኤ.አ በ2030 በአህጉራችን አፍሪካ 2.6 ሚሊዮን ቶን በምግብ ፍጆታነት ሊውል እንደሚችል ጥናቶች ያሳያሉ።

**ስለአዘጋጆቹ**

**ፕራና ኢቨንትስ**

ፕራና ኢቨንትስ ዘርፈ ብዙ የንግድትርዒት እና የቢዝነስ ኹነቶች በኢትዮጵያ ውስጥ በማዘጋጀት እና በማማከር ስራ ላይ የተሰማራ እና ዘርፉን በእውቀት በቴክኖሎጂ እና በግብዓቶች ለመደገፍ ዓለማ አድርጎ የተቋቋመ ኃ/የተ/የግ/ማ ነው። ድርጅቱ ከ10ዓመት በላይ ዓለምዓቀፍ ንግድ ትርዒቶችን፤ ኮንፈረንሶችን እና የቢዝነስ ኺነቶችን በማዘጋጀት ልምድ ባካበተው እና የራሱን አሻራ በጣለው ወጣት ነብዩ ለማ የተመሰረተና የሚመራ ሲሆን፣ ትጉህ፤ እሴት ፈጣሪ እና ለተቀጠሩበት የስራ ቦታ የላቀ ክህሎት ባላቸው ወጣት ባለሙያዎች የተደራጀ ነው። ኢትዮጵያ በዓለም ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እያመጡ ካሉ ሀገራት መካከል ከቀዳሚዎቹ አንዷ እንደመሆኗ ፕራና ኢቨንትስም ሀገሪቱ በንግድ ትርዒት እና የቢዝነስ ኹነቶች ዘርፍ ልታገኝ የሚገባትን ድርሻ ከፍ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ በግምባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ድርጅት በመሆኑ ዘርፉን ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሻገር እና ዘርፋዊ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ኢቨንቶችን ዓለማቀፍ ደረጃን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወኑ በማድረግ የበኩሉን አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ለበለጠ መረጃ፡

ፕራና ኤቨንትስ፡

ላኪ ህንጻ 5ኛ ፎቅ
ፖ.ሳ.ቁ. 16362 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ፡ +251 116 184365
ሞባይል: +251 929 308366
ኢሜይል፡ Nebeyu@fair-team.co
ዌብሳይት፡ http://www.pranaevents.net

**ኤክስፖ ቲም**

ኤክስፖ ቲም ሰርቪስስ ኩባኒያ በዋነኛነት ለአፍሪካ ትኩረት በመስጠት ዐለም አቀፍ አውደ ርዕዮችና ጉባዔዎችን የሚያዘጋጅ ካርቱም ሱዳን የሚገኝ የቤተሰብ ኩባኒያ ነው። በምስራቅና መካከለኛው አፍሪካ በፖልትሪ፣ በፕሪንቲንግ፣ በሲኪዩሪቲና በማሽነሪ ኢንደስትሪዎች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ አውደ ርዕዮችን በማዘጋጀትም የካበተ ልምደ አለው። በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የንግድ ትርዒቶችን በማዘጋጀት ከአካባቢው ጋር የላቀ ትስስር በመፍጠር ተቀባይነቱን ከፍ ማድረግ እና የተወዳዳሪነት አቅሙን ማጠናከር ችሏል።

Expo Team for Service Co. Ltd
Hospital Street, Pantela building, Flat No. 101;
P.O.Box: 13 565 Khartoum 11111, Sudan
Tel: +249 183 745905 Fax: +249 183 745 906
Mobile: +249 912 273795
Email:simsim362002@yahoo.com
Website: www.expoteam.info